

# የተሰባበረው መርከብ

- ጁሊየስ ተብሎ በሚታወቅ አንድ የመቶ አለቃ እዝ ስር በነበረች መርከብ ጳውሎስ ወደ ሮም እየተጓዘ ነበር። በመጀመሪያው መርከቧ በወደብ ስትቆም ጳውሎስ ወዳጆቹን እንዲጎበኛቸው ከጁሊየስ ፈቃድ አግኝቶ ነበር። ወዳጆቹም ለመንገድ የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጡት።

- አሁንም በባህር ላይ ከተጓዙ በኋላ በአንድ ወደብ ላይ ቆይታ አድርገው መርከብ ቀየሩ። በባህር ላይ አውሎ ነፋሱ እጅግ ብርቱ ሰለነበርም መስመራቸውን ይዘው ለመጓዝ በጣም ተቸገሩ። ጳውሎስ አስቀድሞ ይህ የመርከብ ጉዞ እጅግ በጣም አደገኛ እንደሆነ ለመቶ አለቃው ቢነግረውም አልሰማውም። ይልቁን ጉዞው እንዲቀጥል ወሰነ።

- እጅግ በጣም ከባድ ነፋስ መንፈሱን ቀጠለ። መልህቃቸውን ጥለው መጠባበቅ ጀመሩ። ሆኖም አውሎ ንፋሱ መርከቢቱን እጅግ በጣም አናወጣት። የመርከቢቱን ጭነት ለመቀነስም አንዳንድ ዕቃዎችን ባህር ላይ መጣል ጀመሩ። በሶስተኛው ቀንም የመርከቢቱን መቅዘፊያ ባህር ውስጥ ጣሉት። አውሎ ነፋሱም በየቀኑ እየተባባሰ ሄደ። ጳውሎስም ተነስቶ፣ “ይህ እንደሚሆን አስቀድሜ ነግሬያችሁ ነበር፣” በሌሊት ተገልጦለት ስለነበረው መልአክ ነገራቸውና ሊያበረታታቸው ሞከረ። በመርከቢቱ ላይ ያሉ ሰዎች በሙሉ አንዳች እንደማይሆኑም አረጋገጠላቸው።

- አውሎ ነፋሱን ለሁለት ሳምንታት ያህል ችለውት ተጉዘዋል። አሁን ደረቅ ምድር ወደሚገኝበት አካባቢ እየደረሱ ነው። በየጊዜውም የባህሩን ጥልቀት ይለኩ ነበር። በደረቅ ምድር በሚገኝ ውሃ አካባቢ እየደረሱ እንደሆነም ተረዱ። አራት መልህቆቸን በመጣልም መርከቢቱ ወዲህና ወዲያ እንዳትናወጥ ለማድረግ ሞከሩ። ጳውሎስም ሰዎቹን ሁሉ ምግብ እንዲበሉና እንዲበረታቱ ነገራቸው። አስራ አራት ቀናት ሙሉ ምግብ የሚባል ነገር አልቀመሱም።

  ጳውሎስም ምግብ ወስዶ ካመሰገነ በኋላ መብላት ጀመረ።. ሌሎቹም ሰዎች በሉ። ከዚያም በመርከቢቱ ውስጥ የነበረውን እህል አውጥተው ባህር ውስጥ በመጣል የመርከቢቱን ክብደት ለመቀነስ ሞከሩ።

- ጎህ ሲቀድም መሬት አዩ። መልህቃቸውን በማንሳትም መርከቢቱን ወደመሬት በፍጥነት እንድትጓዝ አደረጉ። መርከቢቱ በመሬት ላይ ከነበረ አሸዋ ጋር ስትላተም መሰባበር ጀመረች። በመርከቢቱ ላይ የነበሩ ወታደሮች እስረኞቹ እንዳያመልጧቸው በማሰብ ሁሉንም ለመግደል አሰቡ። ሆኖም ጁሊየስ የመርከቢቱ አዛዥ ማንም እንዳይገድሉ አሳመናቸው። መዋኘት የሚችሉ ወደባህር ዳርቻው እየዋኙ ሄዱ። መዋኘት የማይችሉት ደግሞ ከመርከቢቷ ስብርባሪ እንጨት በመያዝ ተንሳፈው ወደባህር ዳርቻው ደረሱ። ልክ ጳውሎስ እንዳለውም ሁሉም በመርከቧ ውስጥ የነበሩት ከሞት ተረፉ።

- አሁን የደረሱባት የደሴቲቱ ስምም መላጥያ እንደሆነ የአካባቢው ሰዎች ነገሯቸው። በዚያ የነበሩ ሰዎች በጣም ራሩላቸው። በጣም ብርድ ከመሆኑም በላይ ዝናብ ይዘንብ ነበር። ስለዚህ ለእሳት ማንደጃ የሚሆን እንጨት መሰብሰብ ጀመሩ። ጳውሎስም ከተሰበሰበው እንጨት ጥቂት ወስዶ በእሳት ውስጥ ጨመረው። ከእሳት ውስጥም አንድ እፉኝት (እባብ) ከእሳት ውስጥ ወጣችና በእጁ ላይ ተጠመጠመችበት። ነደፈችውም። ይህን የተመለከቱ የደሴቲቱ ሰዎችም ጳውሎስ ከሰራው ወንጀል የተነሳ ከመርከቢቱ ሕይወቱ መትረፍ ቢችልም አሁን ግን ከሞት ሊያመልጥ አልቻለም ብለው አሰቡ። እንደውም ነፍስ ገዳይ መሆን አለበት አሉ። ከአሁን አሁን ይሞታል ብለው ቢጠባበቁም አንዳች የሆነ ነገር አልነበረም። ታዲያ በዚህን ጊዜ ይህ ሰው ሳይሆን አምላክ ነው አሉ።

- የደሴቲቱ አስተዳዳሪ በሆነው በፑፕልዮስ ቤትም እንግድነት ተጋበዙ። የፑፕሊዮስ አባትም ታሞ ተኝቶ ነበር። ጳውሎስም ሲፀልይለት ተፈወሰ። የዚህን ተአምር ወሬ የሰሙ የደሴቲቱ ነዋሪዎችም ሕመምተኞቻቸውን እየተሸከሙ ወደጳውሎስ አመጧቸው። ሁሉም ተፈወሱ። ከሶስት ወር በኋላም የደሴቲቱ ነዋሪዎች ለነጳውሎስ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ካቀረቡላቸው በኋላ እንደገና በመርከብ ጉዞ ቀጠሉ።

*ስለዚህች ስለተሰባበረች መርከብ ታሪክ በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 27፡1 እስከ ምዕራፍ 28፡16 ውስጥ ማንበብ ትችላላችሁ።*

Copyright picture courtesy of gospelservices.com

http://gardenofpraise.com